# ሰው እንደ እላባብ!




ይኸ ሁሉ እሽቅድምድም፤ይኸ ሁሉ ቂም ብቀላ፤

ይኸ ሁሉ ጥንድ ጡንቻ፤ ይኸ ሁሉ ደረቅ ዱላ፤

ይኸ ሁሉ ‘ወታደር’፤ ይኸ ሁሉ ‘ባለመለዮ’ ቀውላላ፤

የከበቧቸው እንደ ጉንዳን ትቢት አንዝረው ሽምላ፤

ተንጠራርተው፤ ተቀራምተው እሚያፈሱት ደም አበላ፤

ጠላት ፈርጀው ወንድማማች አንድ ፍሬዎች ጥንድ ዘለላ፤

እሚራኮቱት ባዶ እጃቸውን በዘረጉ የምህረት ክንድ ጠለላ፤

እነማን ናቸው እኒህ ‘ሰዎች’? የሳውዲ፤ የሂትለር ወይስ የጥሊያኖች ቡችላ፤

ጃዝ የተባሉ ተናካሽ፤ ቅልብ ውሾች የወያኔ ወሮ በላ፤

እንደዚህ የሰው አካል በእንጨት ፈልጦ እጁን በእጁ እሚበላ፤

እውን ኢትዮጵያ? ከሽልሽ ነው ይኸ ሁሉ ጉድ ጭንጋፍሽ በ20 ዓመት የፈላ።

ምን አይተው ነው፤ ምን አግኝተው የዘመቱት በጭካኔ፤

እስኪ እያቸው አስተውለህ፤ እኒህን አረመኔዎች ወገኔ፤

አቤት ባሉ ለታረዱ፤ ለተጋዙ በሳውዲ የሲዖል ምድር ኩነኔ፤

አገር ተመልከት አተኩረህ፤ ጐረቤትም እነዚህን የወያኔ ምስለኔ፤

አጋልጣቸው፤ ሞግታቸው ወላጅ፤ እህት፤ ወንድም ካላቹህ ይኼኔ፤

ግፉ ገንፍሎ ሳያፋጀን ተያይዞ በምድጃችን የብሶት ወኔ፤

**እንያያዝ እጅ ለእጅ እስኪጠፋ ድራሹ ከአገራችን ጠላታችን ወያኔ።**

የጐንቻው! 19.11.13

በሳውዲ ዓረቢይ በምስኪን ስደተኛ ወገኖቻችን ላይ የሚደርሰውን እጅግ የሚዘገንን ግፍ ተቃውሞና ኃዘን በሳውዲ እምባሲ ለመግለጽ በሰማያዊ ፓርቲ የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ ተሰልፈው ሳለ በአረመኔውና በጨካኙ የወያኔ ‘ሶላቶዎች’ በግፍ ለተደበደቡ፤ለታሰሩ፤ለተንገላቱ ጽኑ ወገኖቻችን መታሰቢያ ትሁን።